# ዶ/ር ብርሃኑ አቦ ሂድና ቱሪስት ብላ!!




ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የኛ አርበኛ የዛሬው ሁለ-ገብ ትግል ጠሪ ኽረ እየተስተዋለ!

ድሮ ወጣቶች ሆነን በአሲምባ አብረን የጀመርነውን
የሕዝብ ትግል ጣጥለህ ሄደህ የዚያን ትውልድ ትግል ስትራገም እንዳልተደመጥህ፤

ወያኔ በኢትዮጵያዊነት ላይ የመጣ መዓት ነው ብትባል አልሰማ
ብለህ ከመሰሎችህ ጋር ሽንጥህን ገትረህ ወያኔ ዶሞክራሲያዊ ነው ብለህ አብረህ ከነበረከት
ስምዓን ጋር ውስኪ እንዳልተራጨህ፤ ለኢንቨስትመንት እንዳልተራወጥህ፣

የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት 7ቱ ምርጫ ዘረኝነትን አውግዞ በማያሻማ ሁኔታ ኢትዮጵያዊነትን
በመስዋዕትነቱ ለዓለም ሕዝብ ያረጋገጠበት መሆኑን ረስተህ
ወያኔ የቀረጻትን የዛሬዪቱን ግማደ ኢትዮጵያ ካርታ በእስር ላይ ሆኜ ጻፍኩት
ባልከን የባለብዙ መቶ ገጽ ባዶ መጽሃፍህ ሽፋን ያደረግህ አድር ባይ፤

ቅንጅትን ለመበተን ስንቱን ሤራ እንዳልዶለትክ ዛሬ ደግሞ የግንቦት 7 ድምፅ ብለህ ባወጣኸው
ጋዜጣም ሆነ ድረ ገጽ አርማ ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ማጥፋትህ ማንን ለማስደሰት?

የግንቦቱን ሕዝባዊ አምፅ  አሽመድምደህ ዛሬ ጠመንጃ ልታነሳ?
ለመሆኑ አንተ ማን ሆነህ?

**ያራዳ ቋንቋ ስለሚገባህ አቦ ሂድና ቱሪስት ብላ!!**

**ይቀጥላል**